# ይቅርታ

ከ

አምሀ አስፋው

**የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡**

**Copyright © 1999  Amha Asfaw**

**<u>ሌሎች  መፅሀፎች  (ከደራሲው)</u>**

**ይላላ ደነቦ ..................... ሺ፱፻፹፱ አም**
**የላንግስተን ሂውዝ ግጥሞች.. ሺ፱፻፺ አም**
**በርጫ............................ ሺ፱፻፺፩ አም**

**የፊት ሽፋን - በገና - በ አስራት ወልደ መድህን**

**ለታዬ**

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ማን ይስማቸው! | 09 |
| ኢምፔሪያልዝም! ዬኔ አበባ! | 12 |
| እሮሮ | 14 |
| ምን አሳቃቸው? | 15 |
| መኖር ለመኖር | 16 |
| ወግ | 17 |
| ቆሳቁስስ እነሱ | 20 |
| ሆድ | 22 |
| የአትላንታ ቅንቅን | 23 |
| አልገባንም | 26 |
| ባይተዋር (ለተገኘና ለጉዋደኞቹ) | 28 |
| ታይገር ውድስ | 29 |
| ለላመት ከጎንደር | 31 |
| ሙያ በልብ ነው | 32 |
| ይቅርታ | 33 |
| የአንድ-ወጥነት ፍልስፍና | 34 |
| አድልዎ (ጥያቄ) | 36 |
| አድልዎ (መልስ) | 37 |
| አይኑካ | 38 |
| ደደብ-፩ | 39 |
| ተረት አገር | 40 |
| ደደብ-፪ | 42 |
| ደደብ-፫ | 43 |
| የወደቀ እንጨት ወይም ደደብ-፬ | 44 |
| የወለጋ ገሬርሳ | 46 |
| አስፋው ገብረ አማኑኤል? ወይስ አርች በንከር? | 47 |
| ወዮ!! | 49 |
| የምግብ ሱቅ አጋጣሚ | 50 |
| ምስኪን | 51 |
| የኢንድያናፕሎስ ትዝታ | 53 |
| የእናት ሆድ (ለሙሉጌታ ዘውዴ) | 54 |
| ዋ! ፋሲካ | 56 |

| | |
|---|---|
| ሂዋን | 58 |
| ሳብዬ-ሳባ | 60 |
| የሁለት አጋሰሶች ወሬ | 61 |
| ጉልበት | 63 |
| አጋሰስ | 65 |
| አንበሳ | 66 |
| ማስታዎሻ | 68 |
| ትዝታ | 69 |
| አረንጉዋዴ | 71 |
| ኩነኔ | 72 |
| ምን አለ? | 73 |
| ታውቀዋለህ ካለህ | 74 |
| እኔነቴ | 75 |
| የመኖር ትርጉሙ | 76 |
| ሌብነት እስኪቀር | 77 |

# መግቢያ

ይህ መፅሀፍ ይቅርታ የተባለበት ምክንያት ግልፅ ነው፡፡ ምናልባት ግልፅ ያልሆነ ነገር ቢኖር ለምን ይቅርታ መጠየቅ እንዳስፈለገኝ ሳይሆን አይቀርም፡፡ አንባቢው እንደሚያውቀው፣ ዶክተር ታየ ወልደ ሰማእት የሚዙሪ ዩነቨርሲቲ ተማሪ ነበር፡፡ እኔም የዚሁ ትምህርት ቤት ተማሪም ሰራተኛም ስለነበርኩ፣ ታየን አውቀዋለሁ፡፡ በ ፲፱፻፹፩ አም (፲፱፻፫ አእ) መጀመሪያ ላይ ለጉብኝት ከኢትዮጵያ ተመልሶ መጥቶ ነበር፡፡ ከጎበኛቸው ቦታዎች አንዱ ኮሎምቢያ ነበርና ተገናኝተን ስናወራ፣ ለኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጠኛ ስለሰጠው ቃለ መጠይቅ አነሳሁበት፡፡ የኒውዮርኩ ጋዜዘኛ፣ ታየ አያቶቹ የመጡት ከትግሬ ነው ያለ አስመስሎ ዘግቦ ነበር፡፡ እኔም ታየን «ትግሬ ሳትሆን ለምን ትግሬ ነኝ አልክ?» ብየ ጠየቅሁት፡፡ እርሱም፣ «እኔ እንደዚያ አላልኩም፣ ያልኩት፣ ምን እንደሆንኩ በምን ታውቃለህ፡፡ ለምሳሌ እኔ ትግሬ ልሆን እችላለሁ፤ ነበር፡፡» አለኝ፡፡ ለምን እንደሆን እንጃ፣ አላመንኩትም፡፡ ወይ የኢህደግ አለዚያም የአሜሪካ ቅጥር ነው የሚል ጥርጣሬ ገባኝ፡፡

የአሜሪካ ጋዜጦች ከሚፅፉት እውነት ውሸቱ እንደሚበዛ፤ ታየ ደግሞ ደፋርና አገር ወዳድ መሆኑን የተረዳሁት በጣም ዘይግይቼ ነበር፡፡ ራሴን ከህሊናየ ወቀሳ ለማዳን፣ እግረመንገዴንም ይህችን የግጥም መፅሀፍ ለታየ ለማበርከት እንጅ፣ ተጠራጣሪነቴ ከታየ ክብር ላይ የሚቀንሰው፣ ይቅርታ መጠየቄም የሚጨምረው ነገር አይኖርም፡፡ ለማንኛውም ግን ይቅርታ፡፡

አምሀ አስፋው፡፡
01/01/1999 አእ
ኮሎምብያ፣ ሚዙሪ፡፡

## ማን ይስማቸው! (ለመስፍን ወልደ ማርያም)

ሽማግሌ ሳይቀር ህፃን፣
ወንድ ሳይሉ ሴት ሰብስበው፤
እንደከብት ካንድ ክፍል፤
አስገብተው አጉረው፣
ተባይ እንደሚያጠፋ ሁሉ፣
እሳት ለኮሱባቸው።

ለቅሶአቸውን እየሰሙ ከሩቁ፣
ተንከተከቱ ሳቁ፣
አሽሙዋጠጡ ተሳለቁ።
«ይገባቸዋል!» አሉ፣
ሲቃጠሉ እያዩ፣ ሲጋዩ።
«ይገባቸዋል!» አሉ።

«ጥንትም አረመኔዎች ነበሩ፤
ለትግሬው፣ ለኦሮሞው ያሳዘኑ፤
በእርግጥ አረመኔዎች ነበሩ።
አሁንም ትምክህተኞች ናቸው፣
ጥጋብ ያልሄደ ትትዋቸው።
ስለዚህ መቃጠሉ፣ መጋዬቱ፣
ያንሳቸው እንደሆን እንጅ፣
አይታየንም መብዛቱ።»

ኦሮሞው ዳንኪራ መታ፣
ሀማሴን ትግሬው ጨፈረ፣
«ይገባቸዋል!» አለ፣
በእርግጥ ይገባቸዋል።»

ሰብስበው፣ እጅ እግራቸውን አስረው፣
ረጅም ገደል ፈልገው፣
ጥልቅ አዘቅት መርጠው፣
አስመርጠው፣
ወረወሩዋቸው እንደእቃ፣
ወረወሩዋቸው።

አይቶ እንደማዘን ፋንታ፣
ሰው ሲጠፋ በጅምላ፣
ሰው ሲታረድ በጅምላ፣
ኦሮሞው ዳንኪራ መታ፣
ሀማሴን ትግሬው ጨፈረ፣
«ይገባቸዋል!» አለ፣
ይገባቸዋል፡፡»

ቀኑ መሸ፣ ከዚያም ነጋ፣
አሮጌው አመት አለፈ፣
አዲስ መጣ፤
በግፍ ያለቁት አማሮች ተረሱ፣
አንረሳም ያሉትም ተያዙ፣
ታሰሩ፣ ተገረፉ፡፡
የማይካደውን እስኪክዱ፣
የማይረሳውን እስኪረሱ፤
ወይ ራሳቸው ጠፍተው፣
ሞታቸው እኪሆን መሳቂያ፣
የልበ ቢሶች መሳለቂያ፡፡

ቀኑ መሸ፣ ከዚያም ነጋ፣
አሮጌው አመት ተቀበረ፣
አዲሱም ዝተቱን ይዞ ወጣ፡፡

«ትውልድህ ሀማሴን ነው፣
አካለጉዛይ ሰራዬ፣
አገሬን ጥለህ ውጣ፣
አልፈልግም ላይህ ባይኔ፡፡»

እኒያ ቀላጅ ሀማሴኖች፣
ይመስሉ የነበሩ፣
ያለሀሳብ፣ ያለእንባ የተፈጠሩ፣
እዬዬውን አቀለጡት፣
እሪታቸው አስተጋባ፣

በአውሮጳ፣ በእስያ፣
በአፍሪቃ፣ ባሜሪካ።

አማራው ዳንኪራ መታ፣
ጉራጌ ትግሬው ጨፈረ፣
«ይገባቸዋል እኒህስ»
በእርግጥ ይገባቸዋል።» አለ።

ግን ነገሩ ያስጨነቃቸው፣
የሚመጣው ሲነጋ፣
ከወዲሁ የታያቸው፣

«እረ ብዙም አንጨፍር፣
እረ ተው ጮቤ አንምታ፣
ይዘፈንብናልና እንደዘፈንን፣
ነገ ተራችን ሲመጣ።
ይልቅስ አሻፈረን እንበል፣
አናውቅም የጅምላ ፍርድ፣
የግል ግብሩ ነውና፣
መጥፊያው፣ መልሚያውም የሰው ልጅ።

የእምነታችን መሰረቱ፣
ማረጋገጫው የፅናቱ፣
ምልክቱ የልቀቱ፣
መብታቸውን ሲያስከብር ነው፣
የምንጠላቸውን የነዚያ፣
የወዳጆቻችንን ብቻ ሳይሆን፣
የምንላቸውን የኛ።»

ብለው ጮሁ፣
ማን ይስማቸው፤
መለስ የዘራው በቅልዋልና፣
ኢሳኢያስ የተከለው፣
ማን ይስማቸው!

ሂውስተን፣ ቴክሳስ፣ 12/27/1998 አእ

# ኢምፔሪያልዝም፣ የኔ አበባ

ትንሽ የኦክሲጅን በርሜሎ፣
ይጎትታል በእጁ ይዞ፡፡
የላስቲክ ቡዋንቡዋ፣ ከበርሜሎው ጫፍ ተነስቶ፣
ካፍንጫው ላይ ታስርዋል፣
ትንፋሽ እንዳያጥረው ተብሎ፡፡

አስራ አምስት እጅ ነው የቀረው፣
ከሙቶ፣
ሳምባው አልቆ ተበላሽቶ፡፡

ቢበዛ፣
ሶስት አመት ነው አሉ፣
ትኖራለህ ብሎ፣ ከእንግዴህ፣
የነገረው ሀኪሙ፡፡

እንዲያም ሆኖ፣ በርሜሎውን እየጎተተ፣
ትንፋሽ ሲያጥረው፣ እየቆመ፣
አየሩን በረጅሙ እየሳበ፣
ስራውን ይሰራል፣ በዝምታ፣
ህይወቱ እያለቀ እንዳልሆነ፣
ሞቱ እየቀረበ እንዳልመጣ፡፡

የማተሚያ ቤት ሰራተኛ ነበር፣
በአሲድ የሚያጥብ የፊደሉን ገበታ፣
የሚታተመው ከላይ ፈጦ፣ ቀሪው ገላ እንዲበላ፣
ግን ጨረሰ ሳምባውን፣
እንፋሎቱን ተንፍሶ፣
ላገሩ ሳይሆን ወይ ለራሱ፣
ለጌቶቹ ብልፅግና ብሎ፡፡

በሀምሳ አመት እድሜው፣
የሞት ፍርድ ከፈረዱበት በሁዋላ፣

በዚህ የስቃይ ዘመንህ፣
ልትጠጣ ከፈለግህ ልትበላ፣
በርሜሎህን እየጎተትክ አገልግለን ይሉታል፣
በርሜሎህን እየጎተትክ ስራ።

ምናለ ቢተውት አሁን እንኩዋ፣
ካልጋው፣ ከቤቱ ተኝቶ፣
ቢጠብቅ ሞቱን በተስፋ፤
ምናለ።

የማርክስ ትምህርት፣ አልጥም አለኝ፣
የከበርቴዎቹም እንዲሁ፤
ይኖር ይሆን የተሻለ፣
ስርአቱ፣ ግዛቱ፤
የማላይበት፣ ሰው ሲሰቃይ፣
በአካሉም ሆነ በመንፈሱ።

ይኖር ይሆን?

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፤ 10/17/98 አእ

# እሮሮ

ሞትን ያሸነፈ የለም፣
        አሻፈረኝ ብሎ የቀረ፣
በሰው መሀል በአካል፣
        ከሀይወት በሁዋላ የኖረ።

ግን፣

የሚከነክናችሁ ምክር፣
        የጃፓን ስልጣኔ ሲተረክ፣
ወይም የታላቁ ጴጥሮስ ድካም፣
        አገሩን ካውሮጳ ለማድረስ፣
እሮሮን ስታነቡ የምትሰሙት ዋይታ፣
ዛሬ ላላችሁትም ሆነ፣
    ከእንግዴህ ገና ለሚመጣ፤

የሙት ወሬ አይምሰላችሁ፣
        አፈር ተጭኖት የሚቀር፣
ህያው ቃል ነው የማይጠፋ፣
        ለዘለአለም የሚኖር።

ህይወት እንዳለ ከሞት ወዲያ፣
        የምትጠራጠሩ ካላችሁ፣
ከበደ ሚካኤልን አስታውሱ፣
        እሱ ነውና መልሳችሁ።

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 11/16/98 አእ

# ምን አሳቃቸው?

ጥርሶቼን አግጥጬ፣
አይኖቼን ደግሞ አፍጥጬ፣
ለመሆን ስጥር፣
        ያዬሁትን ዲያብሎስ፣
                ከደብረብርሀን ስላሴ፣

እያዩ፣

ይንከተከታሉ ሴቶቹ፣
እናቴና ሌሎቹ፤

አሁን ምን አሳቃቸው?
ዲያብሎስን ሁን አሉኝ፣
        ዲያብሎስን ሆንኩላቸው፡፡

ታዲያ ምን አሳቃቸው?

---

ናዝሬት 1968-1974 አእ

# መኖር ለመኖር

የእስር ቤቱን መስኮት ተጠግተው፣
        አበሻን አዩ፣ ባሻገር፣
ላይ ታች ሲል፣
        ላይ፣ ታች፣ ለመኖር።

አጥፍቼ ይሆን? አሉ፣
        ወይ ራሴን አሞኝቼ፣
ለመኖር አለመጣሬ፣
ለመኖር አለመኖሬ።

መኖር ከሆነማ ለመኖር፣
እነሱም ኖረናል ይላሉ፣
        እኛም እንላለን፣ አለን።
በጎች ይግጣሉ ከሜዳ፣
        ነገ ፋሲካ መሆኑን እረስተው፣
አህዮችም እንዲሁ፣
        ቁስላቸውን ለዝንብ አጋልጠው።
መኖር ከሆነማ ለመኖር።

የለም! አሉ፣ እንደገና፣ ከትካዜያቸው ነቅተው፣
አበሻ ሲራወጥ ለመኖር።
        በመስኮት ቁልቁል አይተው።

መኖር አይደለም ለመኖር፣
መኖር አይደለም ለመኖር፣
አይደለም።

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 9/21/1998 አእ

## ወግ

*«ተማራኪው ባዙቅ ውሀ ውሀ ሲል፣*
*ዳኘው ስጠው አለ ሰላሳ በርሜል።»*

አላዘዘም ሚኒልክ እንዲገደሉ ጣልያኖቹ፣
እንዲጠፉ እንዲሞቱ፣
ወይ እጃቸው እንዲቆረጥ፣
እንደደንቡ እንደጥንቱ።

የአድዋ ድል ብቻ አልነበረም፣
የሚኒልክ ታላቅነቱ፣
መሀሪነቱም እንጅ ደግነቱ፣
የውርደት ማቅ ያለበሳቸው፣ ጠላቶቹን፣
ኢምንት ያረጋቸው ከፊቱ።

ዋ!

ያጠፋው ሳይጣራ፣ በግል፣
ከዳኛ ቀርቦ፣ ተምዋግቶ፣
ጥፋቱ ጥፋቴ ነው ሳይል፣
ከገደል ተጥሎ ሰው ሲሞት፣
አማራነት ሆኖ ወንጀሉ፣
ወይም ሲባረር ካገሩ፣
የሀማሴን ብጥታት ስለታዬ ከግንባሩ፣
ምን ይል ነበር ሚኒልክ፣
ይህን ጉድ ቢያይ ተነስቶ፣
የባእታ መቃብር ቢተፋው፣
ጊዜና ቦታውን ስቶ፤

ምን ይል ነበር?

ምናልባት፡

ምነው ልጆቼ ምን ነካችሁ፣
ጅብ የነከሰች አህያ ሆናችሁ?
መስሎኝ ነበር ዘመናችሁ፣
ከኛ ይልቅ የሰለጠነ፣
የሰው ወንጀል የግሉ እንጅ፣
የወገኖቹ ያልሆነ።

መብረር አይደለም መሬት ለቆ፣
በብልቃጥ እፅ መበጥበጥ፣
ሰው ግለሰብ መሆኑን ማመን እንጅ፣
የማይታጎር እንደከብት።
መድፍ መስራት አይደለም፣
ፎቅ መገንባት፣ ሀውልት መጥረብ፣
ድል፣ መሀሪነት እንጅ፣
በቀል አለመሆኑን መገንዘብ፤

ያ ነበር የመሰልጠን ምልክቱ፣
ያያት የቅድም አያቶቻችሁ ቅርስ፣
የኢትዮጵያዊነት ምልክቱ፤
ትርጉሙ፤

ያ ነበር።

ይል ይሆን ሚኒልክ፣
መሀሪው ንጉስ፣ ታላቁ፤
ይህን ትውልድ ሲያይ አትኩሮ፣
ከሞት ባሻገር በሩቁ፤
ትውልድ መባሉ አይቀር፣
መቼም ተወልድዋልና ለወጉ።

ታገል ሲባል፣ ፈሪ፣
እርዳ ሲባል፣ ችጋር ጠሪ።
ባልዋለበት የጦር ሜዳ፣
ባልተሳተፈበት ትግል፣

በጅምላ ሊፈርድ ይነሳል፣
        ሰው የበረት ከብት ይመስል።

ትውልድ ይባላል ይህም፣
        እንዳባቶቹ ሁሉ፣
ተወልድዋልና ከናቱ፣
ተወልድዋልና ለወጉ።

---
ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 7/25/1998 አእ

## ቆሳቁስስ እነሱ

ማዶናን እወዳታለሁ፣
        ግን ምን ይሆን ምክንያቱ?
ብየ ሳስብ ሳሰላስል፣
        ከሆነ ወድያ ድርጊቱ፣
ይታየኛል ነፃነትዋ፣
ንፁህ ህሊናዋ፣
        መሰረቱ የድፍረትዋ፣
        መሰረቱ የኩራትዋ፣
ይታየኛል።

የምትፈልገውን ታደርጋለች፣
        የምታምንበትን ሁሉ፣
ሰውን ለማስደሰት አይደለም ግን፣
        ለማስቀየምም እንዲሁ።

አትለምንም ተንበርክካ፣
ስሙኝ ውደዱኝ ብላ፣
ግን ይጎርፋል፣ ህዝበ አለም፣
        ሙዚቃዋን ሊያዳምጥ፣
አብሮ ሊዘል፣ ሊንዘላዘል፣
        ዳንሱን ሊረግጥ፣
        ዳንሱን ሊያቀልጥ።

«የቆሳቁስዋ ኮረዳ» ይላታል፣
        ሲያበቃ ዘሎ፣ ጨፍሮ፣
እንዳልጮኸ ሁሉ፣
        ላንቃው እስኪላቀቅ አብሮ።

እስዋ ግን ገብትዋታል፣
        የረስል ፍልስፍና፣
«ይናከሳል ከፈሩት፣» የሚለውን፣
        «ሰው እንደውሻ ነውና።»

ስለዚህ አታሳይም፣
        የፍርሀት ምልክት፣
የመንበርከክ የመለመን፣
        ህሊናዋን የመሸጥ፡፡

«የቆሳቁስ ኮረዳ» አልዋት!?
        ቆሳቁስስ እነሱ፣
አልለመነች፣ ብላ አድምጡኝ፣
        ዘፈኔን በጅምላ ግዙ፡፡

ቆሳቁስስ እንሱ!!

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 1997 አእ

# ሆድ

ምን አለ ብፅፍ ግጥም፣ ሁሌ፣
ፀሀይ እስክትጠልቅ፣ ጥዋት ጀምሬ፡፡
ምን አለ ብፅፍ፣ 'ምወደውን፣
ምን አለ ባነብ፣ 'ምወደውን፣
ባይኖር ኖር ሆዴ፣
ቢቀር መብላት መጠጣቴ፣
ምናለ፡፡

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 1997 አእ

# የአትላንታ ቅንቅን[፩]

ልዩ ነበር አሰራሩ፣ ፀጉርዋ፣
መሆን አለበት የውበት ምልክት፣ግና፣
እንዲያ ባይሆን፣
እንዲያ አታደርገውም ነበርና፡፡

ቆዳዋ ጥቁር ነበር፣ ያማረ፣
እውነተኛውን ያፍሪቃዊነት ቀለም ያዘለ፡፡
«ትመስላለች ንግስት የምትራመድ ተነስታ፣
ከምስራዊ ሌሊት ከሞተ ከተረሳ፡፡»[፪]
ተብሎ የተገጠመላት፣ ተብሎ የተዘየረላት፣
እስዋ ትሆን ሶስና፣ ቀይ ልብስዋ ያማረባት?

ጥቁር ነበር፤ ልብስዋ እንኩዋ፣
የተሰፋ ሲባል ለስዋ፣
ደርባለች ቀይ ከላዩ፣
እንዳይፋልስ ብላ ይሆን፣
የላንግስተን ሂውዝ ግጥሙ?

ያለም ሰው ትመስላለች፣
ከሩቅ ላያት በጨረፍታ፣
የማይሰማት ጨርሶ፣
የወገኖችዋ ዋይታ፤
ግን የወገኖችዋ ጭንቀት ባይሆን ኖሮ ጭንቀትዋ፣
የወገኖችዋ ምኞት ባይሆን ኖሮ ምኞትዋ፣
ለምን ወጣች ከቤትዋ?
ለምን መጣች አትላንታ?
ለመድህኒት ከጠፋበት፣
እድሜው ከአርባ አመት ያነሰ፣
ምን ፈልጋ ትመጣለች፣
አገርዋን አፍቅራ ካልሆነ?

ልጠይቅሽ አላት አንዱ፣ ተነሳና፣

የ ኦርዌልን[፫] ተረት አስታወሰኝ፣
                የናፖሌዎንን ውሻ፣
ልጠይቅሽ አላት፣

*ለምን ትጉዋዣለሽ፣*
*በሽንጠ ረዥም መኪና፣*
*ምነው አማረ ልብስሽ፣*
*ገንዘብሽ ተዛቀ በቁና?*
*ሀብትሽ ሀብታችን አይደል፣*
*ውበትሽ ውበታችን፣*
*ምኞትሽ ይችላል ሊሆን፣ ምኞታችን?*
*ህልምሽ ደግሞ ህልማችን?*
*መልሺ እስቲ እህቴ፣*
*ጥያቄዬን መልሺ፣*
*እንየው ልብሽን፣*
*ምኞት ህልምሽን አፍሺ፡፡*

እሽ፣ አለች እስዋም፣ የኔ ወንድም፣ እሺ!

*መኅሳቆል አለበት ሰው፣ አካሉ?*
*ይመሰክር ዘንድ ፍቅሩን፣ ለሀገሩ፡፡*

*ነፃ ምድር ማጣት የኮራ ህዝብ ባገሩ፣*
*መፈራት፣ መከበር ያቃተው፣*
*የተደፈረ ድንበሩ፡፡*
*ጉስቁልና ነው ድህነት፣*
*አፍአዊነት የጎደለው፣*
*በማጌጥ በመኩዋኩዋል፣*
*የማይቻለን ልንሸፍነው፣*
*ድህነት ነው!*
*ድህነት ነው፡፡*

*ስለዚህ ህልማችሁ ህልሜ ነው፣*
*ምኞታችሁም ምኞቴ፣*

*የሀገሬ ፍቅር ነውና፣*
*የሚቦረቡረኝ ሌት ተቀን፣*
*ረሀቤ ጥማቴ።*

**ብዙ አይደለምና ቁጥራቸው የውሾቹ፣**
**ወገኖችሽን በሙሉ አትመስይን በነሱ።**
**አታቁዋርጭ ፍቅርሽን ለኢትዮጵያ፣**
**ያ ነውና መመዘኛው ያንችነትሽ መለኪያ።**
**ከመኪናሽ እርዝመት ይልቅ፣**
**ፍቅርሽ ጎልቶ 'ሚታያቸው፣**
**ብዙ ናቸው ወገኖችሽ፣**
**ብዙ ናቸው፤**
**ብዙ ናቸው።**
**ስለዚህ አታቁዋርጭ ፍቅርሽን፣**
**የሀገርሽን አለኝታ፣**
**አንችነትሽን፤**

**አታቁዋርጭ።**

---

**አትላንታ፣ ጆርጅያ፤ 10/11/1997 አእ**
**፩ - ቅንቅን ፡ Ballad (ዶክተር ጌታቸው ሀይሌ።)**
**፪ - ሶስና ቀይ ስትለብስ - ላንግስተን ሂውዝ።**
**፫ - የእንሰሳት እርሻ - ጆርጅ ኦርዌል።**

# አልገባንም

ወያኔ ሲወድቅ፣
የባቢሎን ግንብ ሲናድ፣
ምእራባውያን ሲያሰፈስፉ፣
ትኩስ አምባ ገነን ሊያነግሱ፤

ሊገነጣጥሉ ኢትዮጵያን ፣
በሀይማኖት እያጣሉ፣
በቁዋንቁዋ እየከፋፈሉ፤
ህዝብዋን፣

ማእድንዋን ሊቀራመቱ፣
እኛን ግን ሊያደኸዩ፣
ሊያራቁቱ፣
ሲመጡ፣

ተዋግተን ተፈላልጠን፣
መሳቂያ እንዳንሆን መሳለቂያ፣
የቴሌቪዥናቸው ማሞቂያ፤
ምን ማድረግ አለብን?
ምን መሆን አለብን?

ከአርባ አመታት አስቀድሞ፣
ባይጥና በድመት መስለው፣
ነግረውን ነበር መፍትሄውን፣
አቶ አዲስ አለማየሁ፡፡

ሳይገባን ቀረ ሚስጥሩ፣
ቢፅፉ፣ ቢተርቱ፣
ቢያወሩ፣ ቢናገሩ፣
ሳይገባን ቀረ ሚስጥሩ፤

ሳይገባን ቀረ፡፡

አሁን ደግሞ በጊዜያችን፣
        አቶ መስፍን ወልደ ማርያም፣
መጥፊያ መዳኛችንም ፣
        መሆናችንን እኛው፣
በጥሞና እንድናነበው፣
        ሰጥተውን ነበር ፅፈው፣
ከየት ወዴት ተሰኝተው፣
ከየት ወዴት አሰኝተው፡፡

ግን አሁንም አልገባንም ሚስጥሩ፣

አልገባንም፡፡

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 5/1/1997 አእ

## ባይተዋር (ለተገኘና ለጉዋደኞቹ)

በየቀኑ መሞት አልከው፣
        ለወገን ማልቀስ፣
        ለሀገር ማልቀስ፣
        ለራስክም ማልቀስ።
በመሸ ቁጥር መሞት አልከው፣
        ሲነጋ በታምር መንቃት፣
የመጨረሻ አየርክን መተንፈስ፣
        መዘጋጀት ለመጭው ሞት።

መስጠት ለባዳ፣
        የማይመለስ የልጅነት ጉልበት፣
ማፍሰስ ለባዳ፣
        የማይታፈስ የልጅነት እውቀት፣
ያ ነው፤ በመሸ ቁጥር መፍረስ፣
        ጀምበር በጠለቀ ቁጥር ማለፍ፣
        ጀምበር በጠለቀ ቁጥር መሞት፤
ያ ነው።

ትተኸው የምታልፍ ነገር የለ፣
        አየሩ ላብህን አይቀበል፤
ለሌሎች መስዋእት ሆንኩ አትል፣
        ባእድ ሞትህን አያከብር።

ዋ! መገነዝ በየቀኑ፣
        መባነን ኀህ ሲቀድ፣
ሲመሽ እንደገና ለመድበን፣
        ተመላልሶ ለመፍረስ፤
በባዳ መሀል፣ በባእድ አገር፣
        እውቀትህ ባይተዋር፣
        ጉልበትህ ባይተዋር፣
        ሞትህም ባይተዋር፤
ዋ!!

---
ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 6/2/1997 አእ

# ታይገር ውድስ

ትዝ አለኝ ተማሪ፣
ያዲሳባ፣
ያራት ኪሎው ግቢ፣
የፊዚካ፣
ኤሌትሪከ–መግኒጥነት፣
አጥንተን አጥንተን፤
ከፈተና ስንቀመጥ፣
ይጎናፀፍ ነበር እሱ፣
ዘጠና አምስት ከመቶ፣
ሙሉ ሸዋን ከሰባ፣
እኛን እኛን ካምሳ ትቶ፤

ማን እንደሆን ጠፋኝ ስሙ፣
ግን ትዝ አለኝ ዛሬ መልኩ፣
ዝምታው፣ ጥልቀቱ፣
ትዝ አለኝ ዛሬ፤
እውቀቱ፤

ትዝ አለኝ፡፡

ታይገር ውድስ ሲጨርስ፣
ሶስተኛውን ዙር፣
ሲመራ ከእርከን በታች፣
በ አስራምስት ግብ፣
የማስተርስን የጎልፍ ፍልሚያ፣
የምድረ ነጭ ግብግብ፡፡

ጎልፈኛው ሁሉ፣ አፉን ይዞ፣
የሚያወራው ጠፍቶት አፍሮ፣
ማሸነፍ ሳይሆን ምኞቱ፣
የልይታው ጥበት ሆኖ፣

ከሩቁ ተንጠልጥሎ፣
        ጥጋብ፣ ንቀቱን ደፍቶ፣
ማየቴ፣

ትዝ አሰኘኝ ያን ተማሪ የፊዚካ፣
የት ደርሶ ይሆን አሁን፣ እምንጋ?
የት ደርሶ ይሆን?

አያድርስ ነው አለ፣ አንዱ ጋዜጠኛ፣
ክሪፕቶናይት ከየት እናግኝ፣
        ክሪፕቶናይት ከየት እናምጣ፣
ይህ የመለኮት እንጅ፣
        የሰው ስራ አይደለምና፡፡

መች እንዲህ በቀላሉ፣
ሰው ነው፣ የምትጠሉት፣
        እንደሌላው ጥቁር ሁሉ፣

ሰው ነው፡፡

---
ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 4/12/1997 አአ

# ለላመት ከጎንደር

አልፈግም ላየው ከእንግዴህ፣ ልረግጠው፣
አልፈልግም ልሰማው ዳግመኛ፡፡
ብለው የሚጠሩትን ሲኦል፣
ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ፡፡

ያብርሀም አገር እያለች፣ ያባቴ፣
የሰለሞን ምድር ፣
የጠቢቡ ንጉሴ፣
ማር የሚቆረጥባት ወለላ፣
ወተት የሚፈስባት እናቴ፡፡

እየሩሳሌም መዲናየ፣
ወርቅ የተነጠፈበሽ፣
እየሩሳሌም መዲናየ፣
አልማዝ የሚለቀምብሽ፣
እየሩሳሌም መዲናየ፣
እኩልነት የሰፈነብሽ፣
እየሩሳሌም መዲናየ፣
ፍቅር የነገሰብሽ፤
እየሩሳሌም መዲናየ፤
.
.
.
ምነው እየሩሳሌም!
አለ እንዴ ጥላቻ፣
አንችምጋ?
ወይስ መጣሁ መንገድ ስቼ፣
እየሩሳሌሜን ትቼ?

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፤ 4/1/1997 አእ

# ሙያ በልብ ነው

የሚያቃጥላቸው፣
ውድቀትዋ ያገራቸው፣
እንዲያም ሆኖ፣
ይታየኛል መኖራቸው፣
የማይችሉ መለገስ ባደባባይ፣
የማይጠራ ስማቸው፤
ይታየኛል ችግራቸው፤
ይታየኛል መኖራቸው፤
ይታየኛል።

ግን ሌሎች አሉ፣
ባደባባይ መስጠት ሲችሉ፣
የሚነተቱ ከመሬት፣
በልባቸው የሚሳቡ።

ቦታ አለው፣
መሆኑ በልብ ሙያ፣
የቸሩትን አለማውራቱ፣
አለመመፃደቅ በይፋ።

ግን ባሁኑ ዘመን፣
ባለንበት ሁኔታ፣
አይገባኝም ሙያነቱ፣
ስም ሳይገልፁ ስጦታ፣
ለመብላት ካልሆነ በቀር፣
በሁለት ጠርዝ፣
ካሽናፊው ለመቡዋደን፣
ሁዋላ ለመስረቅ ለመዝረፍ።

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 3/27/1997 እአ

# ይቅርታ

ይቅርታ ልጠይቅህ፣ ታየ፣
ጠርጥሬህ ነበርና፣
የነዚያ ሰው ነህ ብየ፡፡
ይቅርታ አድርግልኝ፣ ታየ፣
ጠርጥሬህ ነበርና፣
የነዚህም ሰው ነህ ብየ፡፡

ለካስ የማትገዛ ኖረሀል፣
ለህሊናህ ካልሆነ፣
ለካስ አትንበረከክም አንተ፣
ለእናት አገርህ ካልሆነ፣
ምንኛ ስቼ ነበር እውነትን፣
ምንኛ ስቼ ነበረ፡፡

እንኩዋስ ስለሌላ፣

እንዲህ ነበርኩ እንጅ፣
እንዲህ እሆናለሁ ብየ፣
እንዲህ አረግሁ እንጅ፣
እንዲህ አደርጋለሁ ብየ፣
ስለራሴም አላወራ፣
ከእንዴህ ወድያ ደፍሬ፡፡

ይቅርታ፡፡

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 2/13/1997 አእ

# የአንድ-ወጥነት ፍልስፍና

አሁን መርጋቱ፣
ዛሬ መፅናቱ፣
በመሆኑ ነው፣ የትናንት ውልድ፣
ያልተናጋ መሰረቱ።

አብዮት ባፈረሰው ዛሬ ላይ፣
ውሸት በፈጠረው አሁን ላይ፣
ነገን እመሰርታለሁ ማለት፣
ዘበት ነው፣ ዘበት።

ካላችሁ እንፍጠር ነገ፣
የረጋ፣
ተመልሳችሁ ወደሁዋላ፣
ቆፍራችሁ፣ አውጥታችሁ፣
የረጋ ዘመን የፀና፣
ዛሬን መስርቱ በዚያ፣
እንዲቆም ነገ እንዲረጋ።

አለዚያ ግን፣
ጨዋታ ነው፣ ጨዋታ።

ማለት አይደለም፣ አይታረም፣
ትናንት፣
የኀበጠው አይቅና፣
የበሰበሰው አይቆረጥ፤

ግን ትናንትን ደምስሶ በጅምላ፣
ነገ ለመፍጠር መርዋርዋጥ፣
የፀና፣
ከንቱ ልፋት ነው፣ መና፤

ከንቱ ልፋት ነው።

እንኖራለን እንጂ፣
ስንታመስ፣ ስንቆላ፣
ነገ እንደሁ አይቆም፣
አይረጋ፣
ከትናንት ካልተወለደ፣
ከዛሬ ማህፀን ካልወጣ፡፡

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 1/26/1996 አእ

# አድልዎ (ጥያቄ)

እናት፣
ተረፍርፎ ብታይ፣
ጡት የጠማው ህፃን ከሜዳ፣
የራስዋን ልጅ ሳትመግብ፣
የራስዋን ልጅ ሳታጠባ፣
ዞር ብላም አታይ ሌላ።

የሚጠይቃት የለም፣
እንድታደርግ እንዲያ፣
የሚያወግዛትም አይኖርም፣
አልሰጠችም ብሎ፣ ወተትዋን ለባዳ፤
ባዳም አይጠይቅ ደፍሮ፣
ልጅሽን ትተሽ፣ እኔን አጥቢኝ ብሎ፤
አይጠይቅም ደፍሮ።

ታዲያ! ለምን ይሆን ሰው፣
ለወንዙ፣ ለመንደሩ፣
ለጎሳው፣ ለሀገሩ፣
ለቀለሙ፣ ለዘሩ፣
ሲያደላ፣
እንደነውር መቆጠሩ፣
«ሁዋላ ቀር ነው» መባሉ፤
ለምን ይሆን?

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፤ 1/26/1996 አእ

# አድልዎ (መልስ)

እናት፣
ተረፍርፎ ብታይ፣
  ወተት የጠማው ህፃን ከሜዳ፣
የራስዋን ልጅ ሳትመግብ፣
  የራስዋን ልጅ ሳታጠባ፣
ዞር ብላም አታይ ሌላ።

ግን፣ የሌላ እናት ልጅዋን ጥላ፣
የስዋን ብቻ እንድታጠባ፣
ካደረገች አስገድዳ፣
አድልዎ አይባልም ይሄ፣
  ሌብነት እንጅ ዘረፋ።

ባዳም ይቃወማል ደፍሮ፣
ልጄን ሳላጠባ ልጅሽን አላጠባም ብሎ፣
ይቃወማል ደፍሮ።

ታዲያ! ለዚህ ነው ሰው፣
  የሌላውን ሰርቆ፣ ለወንዙ፣ ለመንደሩ፣
  የሌላውን ነጥቆ፣ ለጎሳው፣ ለሀገሩ፣
  ሌላውን ገድሎ፣ በድሎ፣ ለቀለሙ፣ ለዘሩ፣
ሲያደላ፣
  እንደነውር መቆጠሩ፣
  «ሁዋላ ቀር ነው» መባሉ፣
ለዚህ ነው።

---
ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 2/2/1996 አእ

# አይኑካ

ካለም በቃኝ ካጥር ወዲህ፣
        ካለም በቃኝ ካጥር ወዲያ፣
ተቀምጦ፣
        ተቀምጣ፣
አይንዋን ተክላ ባይኑ፣
        አይኑን ተክሎ ባይንዋ፣
እስዋ ሆና የሱ አይኑካ፣
        እሱም ሆኖ የስዋ … የስዋ …. ፡፡

ፍቅር ጠባዩ የስበት ነው፣
        ተፈጥሮውም የጨረራ፣
እርቀት አያግደውም፣
        አጥር አይከላውምና፡፡

ንክኪት የፍቅር መግለጫ አይደለም፣
        ምነው ስንቱ ተነካክቶ፣
አገር ምድሩን በሰው ሞልቶ፣
ያድር የለ ፣ ይውል የለ፣
        በጥላቻ ተቆራምዶ!

የስበት ፍቅር፣ የማዶ ፍቅር፣
ባይን የሚገባ ጨረራ፣
መፅናኛ በለቅሶ ዘመን፣ በዋይታ፣
አይኑካ፡፡

---

ዋሽንግቶን ዲ.ሲ፣ 7/6/1996 አእ

# ደደብ-፩

አለቀ መሰለኝ ጉዞው፣
        ተዘጋ መሰለኝ መንገዱ፣
ስልጣን ላይ የመንጠልጠሉ፣
        ፈላጭ ቆራጭ የመሆኑ፡፡

ከሞተ ፳ አመት ያለፈው፣
        ፈልጎ ጠላት የወደቀ፣
አትገላግሉኝ ማለት፣
        ካልተዋጋሁ ጦርነት ያለቀ፣
                የደቀቀ፤
አንድም ነው ፈሪነት፣
አለዚያም ደደብነት፡፡

ደደብ!!

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፤ 7/18/1995 አእ

# ተረት አገር

ተረት ተረት፣

ከልጆች መሀል አንዱ፣
        ያለው ጠንከር፣
አለና ወሰነ፣
        «እንጫወት! አገር አገር።»

ከዚያም፣

«እኔ ንጉስ፣
        አንተ ሾፌር፣
እሱ ወታደር፣
        እስዋ ዶክተር፣»
አለና ዘረገፈው ይህን ሹምሽር።

«ልጆቼን ሆዴን» ብሎ፣
        ደሞዙን ጠየቀ፣ ወታደር፣
«ተሰበረ፣» አለ «መኪያዬ፣»
                        ሾፌር፣
«ማዳን መፈወስ እንጅ ስራየ፣
        መች ሆነና መገነዝ መቅበር፣»
ብላ አጉረመረመች፣
                ዶክተር።

አልጫወትም አለ ገመሩ፣
                አኮረፈ ንጉሱ፣
ያውቃሉና ክትለቱን፣
        ልጆቹ ፈሩ፣ ታመሱ።

ስለዚህ፣
        «እንግዴህ ምን እንጫወት?
የምንወደው የምናውቀው፣
        የለመድነው ያደግንበት?»

ብለው ጠየቁ ንጉሱን፣
እንደማያውቁ ሁሉ መልሱን።

«ሌባና ፖሊስ፣» አለ ንጉሱ፣
ጥርሱን ገልጥጦ እስኪታይ ድዱ፣
እንደተገለፀለት ሁሉ ጥበቡ፣
የልጅ ጨዋታ ሚስጥሩ፤

«አንተ ሌባ፣ እኔ ንጉስ፣
እስዋ ዳኛ፣ እሱ ፖሊስ።»

ደስ አላቸው ልጆቹ፣ ፈነጠዙ፣
ወደደቡብ ወደሜዳው፣ ተያይዘው ወረዱ፣
ሌባና ፖሊስ ሊጫወቱ።
አንዱ ንጉስ፣ አንዱ ሌባ፣
አንዱ ፖሊስ፣ አንድዋ ዳኛ፣
እየሆኑ . . . . .

እንግዴህ ተረቴን መልሱ፣
አፌን በዳቦ አብሱ።

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 7/30/1995 አእ

# ደደብ-፪

መስለኸኝ ነበር ዘረኛ፣
የዘመኑ ብልጥ ተንኮለኛ፣
ማረኝ ጌታዬ ይቅርታ፣
አንተስ ደደብ ነህ ለካ፡፡

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 7/18/1995 አእ

# ደደብ-፫

መስለኸኝ ነበር ዘረኛ፣
የነዚያ ሰው ተንኮለኛ፣
ማረኝ ጌታዬ ይቅርታ፣
አንተስ ወገን* ነህ ለካ፡፡

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 1/20/95 አእ
*ደስታ ተክለ ወልድን ተመልከት፡፡

# የወደቀ እንጨት ወይም ደደብ-፩

አምዋቸው ነበርና፣ ደጃዝማቹ፣*
ህልማቸው ጎልቶ፣ ደብዝዞባቸው እውነቱ፡፡
እንዲያም ሆኖ፣
መጥፎ አልነበረም ህልማቸው፣
ላሽከሮቻቸው ማዘናቸው፣
ላሽከሮቻቸው ማሰባቸው፣
መጥፎ አልነበረም፡፡

አሁን ምኑ ነው ተንኮሉ?
የት ላይ ይሆን ክፋቱ?
«ርስቴን ሸጣችሁ፣
ደሞዛቸውን ጨምሩልኝ፡፡» ማለቱ፣
ኧረ ምኑ ላይ ነው ስተቱ?

ልብማ ቢሆርህ ኖሮ፣
በበታችነት ስሜት ያልተሞላ፣
«እንዲህ አይደለም ነገሩ፣
አባባ፣
ርስት ያለው ሰው የለም አሁን፣
የሁላችን ሀብት ሆንዋል፣ የጋራ፣
ገባርነትም ቀርትዋል፣
የሰው ልጅ እኩል ነውና፡፡»
ትላቸው ነበር በጥሞና፡፡

ግን አመታት ካለፉ ወዲያ፣
መሞከርህ ልትዘልፋቸው፣
ልትስቅ፣
ልትሳለቅባቸው፤
መሆኑን ነው የሚገልፅ፣
የተፈጥሮህ መሰረት፣
ይሉኝታ ያልጎበኘው፣
ቅሌትና ቀላልነት፡፡

የሚከተለውን እንኩዋን፣
        አልፈልግም ነበር ልፅፈው፣
ግን እንዳንተ ያለ ደደብ፣
        አይገባውም ካልተነገረው፡፡

ያኔ፣

ካልቀረ መልከስከስህ ከዚያ፣
ያገልግላቸውን ትራፊ ልትበላ፣
ምናለ ብትነግራቸው፣
«እውነታው ሌላ ሆንዋል፡፡» ብትላቸው፣
አልጋቸውን ስታነጥፍ፣
        እግራቸውን ስታጥባቸው፣
ምናለ ብትነግራቸው፡፡

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 7/18/1995 አእ

*በለጠ ሙትሮ የተባለ የዘር ፖለቲከኛ ከደጃዝማች አምሀ አበራ ጋር አብሬ ታስሬ ነበር ብሎ ለሰነዘረባቸው የማያስፈልግ ዘለፋ፣ መልስ፡፡

# የወሊጋ ገሬርሳ*

አንጠጣም ጠላ፣
ጠጁ ምን ሆነና፣
አንበላም ሽሮ፣
ጮማው ተከምሮ፣
አጠጡት ለኢሀደግ፣
        አብሉት ለወያኔ፣
ሽሮ ላረረበት፣
        ላልለቀቀው ጠኔ፡፡

---

ኮሎምብያ ሚዙሪ፣ 1993 አእ
*ሀሳቡ የተወሰደው ሰለሞን አንጋሼ (Dr. Solomon, B. Ungashe) ከኦሮምኛ ተርጉሞ ከፃፈው የወሊጋ ገሬርሳ ነው፡፡

# አስፋው ገብረ አማኑኤል
# ወይስ አርቺ በንከር?

ህብረ ትርኢት ስናይ፣ ሀሙስ ማታ፣
ቤተሰቡ በሞላ፣
አጃቢዎቹ ሲረግጡ ዳንኪራ፣
እጥፍ ሲሉ ዘርጋ፣ እንዳለንጋ፣
ሴቶቹ ሲደንሱ ያይና፣
አባቴ በፈገግታ፣
ይላል፣ «ተመልከትዋት ሲያምርባት፣
        ስትውረገረግ ስትቀናጣ፣
ተመልከትዋት፡፡

ጉድ እኮ ነው ወገብዋ፣
የት ሄደ ይባላል አጥንትዋ፣
ስትሾር እንደ እንዝርት፣
ስትፍለቀለቅ ስትስቅ፣
ተመልከቱት ውበትዋን፣
ተመልከቱ ደስ ማለትዋን፡፡»

እንዲያ ሲያደንቅ ሲደሰት፣
        በቴሌቪዥን ጨዋታ፣
እናቴ አንዳንዴ፣
        ባይንዋ ጥግ ታየውና፣
«ድንቄም!» ትላለች፣
        ሌላም ብዙ አታወራ፡፡

ከዚያም፣
የወንድ አጃቢዎች ይገባሉ፣
                ከመድረኩ፣
እየጨፈሩ፣ እየተውረገረጉ፣
        እነሱም እንደሴቶቹ ሁሉ፡፡

ያ ስለያንዳንድዋ ዳንኪረኛ፣
        አስተያየት ሲሰጥ የነበረ አባቴ፣
ይኮማተራል ግንባሩ፣
        ፈገግታው ይጠፋል ባንዴ።

ሁላችንም ዝም እንላለን፣
አዲስ ነገር ለመስማት አይደለም፣
        የሚለውን እናውቀዋለን።
ዘፈን ካለ ጭፈራ፣
የማይቀር አስተያየት ነው፣
        የሚደገም ሀሙስ ማታ።

እሱም እንደኛ ሁሉ ዝም ብሎ፣
ይቆይና፣ በወንዶቹ ሁኔታ አዝኖ፣
«ሀይለስላሴ ይሙት!!» ይላል ጮሆ፣
«ይሄን ሁሉ ስራ ፈት፣ ይሄን ሁሉ ባለጌ፣
ቢፈቅዱልኝ ጃንሆይ፣
        በግር ብረት ቀፍድጄ፣
ጤፍ አሳርመው ነበር፣
        ምንጃር ከእርሻየ ወስጄ።

ተመልከቱት ሲያውደለድል!
ተመልከቱት ሲያዘጠዝጥ!
ተመልከቱት · · · · · !
ተመልከቱት · · · · · !»

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 09/6/1995 አእ

## ወዮ!!

ላባቶቻችን፣
        ርህራሄ ነበር፣ የጀግንነት ምልክቱ፣
ድል ለሆነው ሰራዊት፣
        የልባቸውን ሰፊነት ማሳየቱ።

የዘመኑ አድራጊዎች፣ ድል፣
እንኳዋንስ ኖሮ የተፈፀመ በደል፣
ያልነበረም ቢሆን እየፈጠሩ፣
ያሳዝናል ማየቱ፣ ሲገሉ፣ ሲበቀሉ።

ድል ይሆናል፣ ድል አድራጊ፣
ያሸንፋል መልሶ፣ ተሸናፊ።
የሚያሳዝነኝ መጥፋቱ፣
የሚያስፈራኝ ሳስበው መቅረቱ፣
ከድል በሁዋላ በቀል፣ የፈሪ ጠባይ መሆኑ፣
ያባቶቻችን ደግነት ነው፣
        ላሸነፉት ህዝብ መራራቱ።

ይሄ ነው 'ሚያሳዝነኝ፣
                መጥፋቱ መረሳቱ።

ትውልድ፣ ከቀደመው ነውና የሚማር፣
መሀሪነት ከሆነ ነውር፣
በቀል ከሆነ የድል መኸር፣
ወዮላቸው ለባንዶች አገራቸውን ለሸጡ፣
ወዮላቸው ለነዚያ ከእንግዴህ ድል ለሚሆኑ።

ወዮላቸው!!

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 9/8/1995 አእ

# የምግብ ሱቅ አጋጣሚ

«በላይም በታችም፣ በግራም በቀኝም፣
እኛው ነን ገዥዎቻችሁ፣
እኛው ነን ጌቶቻችሁ፣
ለሚከተሉት ፴ አመታት፣
        ወደዳችሁም ጠላችሁ፡፡

ትግሬ ነው» አለኝ «የሚገዛህ፣
        ሸዋም ኖርክ አስመራ፣
የሚኮረኩምህ ለዘመናት፣
        ሲዳሞም ገባህ ወምበራ፡፡»

ይሄ ጥጋብ፣ ይሄ ትእቢት፣
        እንኩዋን ላንተ፣
ዘንግተኸው ይሆናል እንጅ፣
        ለጌታህ ለቹሊም አልበጀ፡፡

ግን፣

ለወሬው ያህል ለነገሩ፣
ይሄው ነበር ችግሩ!
ያ ሁሉ ህዝብ ያለቀበት፣
        ያ ሁሉ ሀብት የፈሰሰበት ሚስጥሩ!

ይሄው ነበር ችግሩ!
ይሄው ነበር ሚስጥሩ!
ይሄው ነበር ·····!
ይሄው ነበር ·····!

---

ኮሎምቢያ ሚዙራ፣ 09/26/1995 አእ

# ምስኪን

አለሁ ስትል ከማህበር፣
ቆመህ ከዳር፣
ህብረሰቡ ጥሎህ ባንድ አቅጣጫ፣
አንተ በሌላው ስትዳክር፣
ምስኪን!

ትደርስባቸዋለህ አይባል ነገር፣
መንገዳችሁ አንፃር ላንፃር፣
ልባችሁ እየተራራቀ፣
አለማችሁ እየተላቀቀ፣
በሄደ ቁጥር፣
ሁለት አለም ፈጥረው፣
የጭንቁን አለም ላንተ ሰጥተው፣
ትተው፣
«አዬ ጉድ» ይላሉ፣
«ምን መአት መጣበት፣
ምን ቁጣ ላከበት፡፡»
መአቱን እነሱው አምጥተውብህ፣
ቁጣውን እነሱ ልከውብህ፡፡
ምስኪን!

የነሱ ነገር አይመጣልህ፣
ለፍቅራቸው አትታደል፣
ከውበታቸው አይደርስህ፣
ነፃነታቸውን አትካፈል፡፡

ብቻ፣
የሀዘናቸው መወጫ፣
የእንባቸው መረጫ፣
የጥላቻቸው መዝገብ፣
የውበታቸው መመዘኛ፣

የያዙትን ማክበሪያ ነህ፣
አምላካቸውን ማመስገኛ፡፡
ምስኪን!

ግን፣
አለም ያለችው በሚዛን ነው፣
ውጥንቅጥዋም በመለኪያ፣
ህልውናዋ ነውና፣
ካልሆነች የለችም እንዲያ፡፡

ታዲያ አንተን ምስኪኑን ምን ይዋጥህ?
ሚዛኑ ሲያንጠለጥልህ፣
መለኪያው ኢምንት ሲያደርግህ፣
ምን ይዋጥህ?

ከቻልክ፣
ፍቅራቸውን፣
ደስታቸውን፣
ወይ ትገዛለህ፣
ወይ ትነጥቃለህ፤

ካልቻልክ ደግሞ፣
ሲያለቅሱልህ ታለቅሳለህ፣
ሲስቁልህ ታለቅሳለህ፣
ሲስቁብህ ታለቅሳለህ፣
ምስኪን!

---
ጀፈርሰን ሲቲ ሚዙሪ፡፡ መስከረም 1974 አእ

# የኢንድያናፖሎስ ትዝታ

## <u>ሳንዲ ፩</u>

ፀጉርዋ ወርቃማ ነው፣ ቆዳዋ ጨምዳዳ፣
አርጅታ 'ማታረጅ፣ አፍዋ 'ማይገታ፡፡
አእምሮዋ የዛገ፣ ወይ ጥንትም ያልጠራ፣
አይ ወይዘሮ ሳንዲ፣ የምላስ ደብተራ፡፡

## <u>ሳንዲ-፪</u>

ትለፈለፋለች፣ የላትም የምትለው፣
ታወራለች ታናፋለች፣
        የሚገባ ነገር ለጆሮየ አይደርሰው፣
ይበዛል አዳማጭዋ፣ ስትናገር፣ አፍዋን ስትከፍት፣
የ EPA ባለስልጣን ናትና፣
        ማስቀየም አይቻል ሳንዲን፡፡

## <u>ተስኪ</u>

እንደሳንዲም ባይሆን፤
        ምላሱ ረጅም ነው የተስኪ፣
እንደሳንዲም ደደብ ባይሆን፣
        እውቀቱ እምብዛም ነው የተስኪ፣
አይ የፕሪንስተን ተማሪ፣
        ድንቄም ያይነስታይን ንክኪ፡፡

---

ኢንድያናፖሎስ ኢንድያና፤ 1994 አእ

## የእናት ሆድ (ለሙሉጌታ ዘውዴ)

ኢትዮጵያ!
        የተጠሙልሽ የተራቡልሽ፣
        የታመሙልሽ የቆሰሉልሽ፣
ልጆችሽ፤

እንደመስማት ድምፅሽን፣
እንደማሽተት አየርሽን፣
        አሁንም ላንች ብለው፣
        ከምድር ዳር ተገልለው፣
        እንዳይወድቁ ምድርን ስተው፣
        አንችን ጥለው
                አንችን ትተው፤

ተንጠልጥለዋል በጥፍራቸው፣
        የሙጥኝ ብለው ጠርዙን፣
ከመሬት ጥግ ከዳርቻው
        ተግዘው ታስረው በቁም፡፡

ምነው የሚወዱሽ አለቁ?
ምነው ተፈረዳባቸው ተጋዙ?

አጠገብሽ ካሉ፣
        እንዳይሞቅሽ ይሆን ትንፋሻቸው?
ፈሪ ልጆችሽ፣
        እንዳይሸበር ልባቸው?
እንዳያገግም፣ እንዳይነሳ፣
        ከሞት እንዳይተርፍ፣ ወኔያቸው?

ጀግኖች ልጆሽ አለቁ፣
አልባሌ ቦታ ወደቁ፡፡
ፈሪ ልጆችሽ ሸሹ፣
የፈረንጅ ፍርፋሪ ለመዱ፡፡
ሌቦች ልጆሽ ብቻ ቀሩ፣

ጉያሽን ሊቦጠቡጡ፣
ስጋሽን ሊቀራመቱ፡፡

ምነው የሚወዱሽ አለቁ?

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 07/09/1995 አእ

# ዋ! ፋሲካ

ምግብ ሲሰራ ሌሊት፣ ለፋሲካ፣
እጠብቅ ነበር ተቀምጬ፣ ከናቴ ጋ፡፡

የቤቱ ሰው ተሰብስቦ ከማድቤት፣ እያወጋ፣
ቡና እየተፈላ እየተጠጣ፣
እንጀራው ሲጋገር፣ ዶሮ ወጡ ሲቁላላ፣
ማድቤቱ ሲታፈን፣ በቁሌት በቅመም ሽታ፣

እውነቱ ተረቱ፣
        ቅጥፈቱ፣ ፍጥረቱ፣
ተደባልቆ ሲተረክ፣ ተደባልቆ ሲወራ፣
አፌን ከፍቼ ሳዳምጥ፣
        ስጠብቅ ፋሲካን በተስፋ፣
እንቅልፍ ይዞኝ እልም ይላል፣
        ከተቀመጥኩበት ሰሌን ሳልነሳ፡፡

ዋ! ፋሲካ፣

እንዲያ ነበር ፋሲካ፣
እድሜየ ፲ እስኪሞላ፣
ሁዋላ ግን እንዳልባል የሴት ልጅ፣
        ሰው የማይሆን የማይረባ፣
የቤቱ ሰው ተሰብስቦ ከማድቤት ሲያወካ፣
እኔ ከመኝታየ፣
        ተቀስቅሼ እስክፈስክ፣
        ተቀስቅሼ እስክበላ፡፡

፲፯ ሞላ እድሜየ፣
ማድቤቱ ተረሳ፣
        እንዲሁም አልጋየ፣
ዙላ አሪዞና፣
ስዊዝ ካናል ቀበና፣

ነፋስ ስልክ ሎስ አንጀለስ፣
ካዛንችስና ላስቬጋስ፣
በረሀው የደጃች ውቤ፣
ሆነ ቤቴ፣ በተስኪያኔ፣
መፈሰኪያየ፣ መፀለያየ፣
ለዚያ ላደረሰኝ አምላክ፣
ምስጋና ማቅረቢያየ።

እንዲያ ነው እንጅ ፋሲካ፣
የወንድ ልጅ ፋሲካ፣
እንዲያ ነው እንጅ የጨዋ ልጅ፣
ሰው የሆነ የረባ።

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 10/1/1995 አእ

# ሂዋን

ትልቅዋን ማለቴ አይደለም፣ ትንሽዋ፣
በሰው አገር ያደገችው፣
በሰው አገር ተወልዳ።

ጨዋታቸው በሚከነክን፣
ቀልዳቸው አጥንት በሚሰብር፣
በነጮች አገር መወለድ፣
መኖር፣
አላገዳትም ከመማር፣
ቋዋንቋዋን ከመፃፍ፣
ቋዋንቋዋን ከመናገር፤
አላገዳትም።

አላገዳትም ከመረጨት፣
የአባን ጠበል፣
ስብከታቸውን ከመስማት፣
መስቀላቸውን ከመሳለም፤
አላገዳትም።

አንዴ፦
ሂዋን ጫማዋን ሳታወልቅ፣ ዘላ፣
ከበተስኪያን ገባች፣ ሰተት ብላ፣
የተናደደች አበሻ፣
የሂዋንን እጅ ይዛ፣ ጎትታ፣
አነበበችላት የተፃፈ ጥቅስ፣ ከግድግዳ፣
በትልቁ፣ በአማርኛ።

*የተባረከ ነውና የቆምክበት መሬት፣*
*ጫማህን ሳታወልቅ አትርገጠው፣*
*ጫማህን ሳታወልቅ አትቁምበት።*

አዳመጠችና ሄዋን፣ በጥሞና፣
ትርጉሙን አሰላስላ፣ አማርኛውን አጢና፣
ፈገግ አለች፣
ድል የሰዋ መሆኑ ገባትና፡፡

«ታዲያ እኔ» አለች ሄዋን፣
አንጋጣ እያዩች የተቆጣቻትን አበሻ፣
«አንች ነኝ እንጅ ሴት፣
መች አንተ ተባልኩና! »

አላገዳትም፣ ከመመርመር፣
የአማርኛዋን አሰካክ፣
የወገኖችዋን የእምነት ሚስጥር፣
በባእድ አገር መወለድ፣
በባእድ አገር መፈጠር፣

አላገዳትም፡፡

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 02/24/1996 አእ

# ሳብዬ-ሳባ

የኢትዮጵያ ንግስት ናት አሉ! ሳባ፣
ምነው ቢቀርብን የኛነትዋ፣
አረብ ቢሆን ትውልድዋ፣
የመን ቢሆን ግዛትዋ፣
ምነው ብትቀርብን፣
        በፍንጫችን ብትወጣ።

ያላዩችውን ወንድ ፍለጋ፣
ያለ የሌላትን ጭና፣ አስጭና፣
አገረ አቁዋርጣ በሄደች ቅንዝረኛ፣
አይገባኝም ለምን እንደምንኮራ፣ እኛ።

ላሉባልታው፣

ለምን ይሆን ንግስቲትዋ፣
እንዲያ መሆንዋ፣
        እንዲያ ማድረግዋ?
ምናልባት፣ ወንድ ጠፍቶ ይሆን ባገሩ፣
እንዳለንበት ዘመን ሁሉ?

---

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 2/28/1996 አእ

# የሁለት አጋሰሶች ወሬ

አጋሰስ-፩፡ ዛሬ ጌታ አፈወርቂ ምን አሉ?

አጋሰስ-፪፡ «ወርቁዋን ብርዋን ሰርቄ በሞላ፣
አንጀት ሆድ-እቃዋን ሁላ፣
ከምድር በታች ያለውን፣
ጊዜ ያስቀመጠውን፣ ጊዜ የቀበረውን፣
የሚንቀሳቀሰውን ከላይ፣ የበቀለውን ፍሬ፣
አበሻ ላቡን አፍስሶ፣ ያቆዬውን ለልጁ፣
ያኖረውን ለዛሬ፣
እቀራመታለሁ» አሉ፣
«ከጌቶቼ ጋር አብሬ።»

አጋሰስ-፩ እኛስ ምን እንበል?

አጋሰስ-፪ ደስ ይበልህ አበሻ፣ ባለም ያለህ ሁሉ፣
ወርቅህ መዳብህ ብርቅ ሆነ፣
ፈረንጅ ወደደው አሉ።
እልል በይ ኢትዮጵያ፣
ጮቤ ምቺ፣ ጨፍሪ፣
ምስጋና አቅርቢ ለመለስ፣
ምስጋና አቅርቢ ላፈወርቂ፣
አፍኖት የነበረውን ሀብት፣
ንቆጉ ሀይለስላሴ፣
አልሰጥም ብሎ ለፈረንጅ፣
ሳይሰለጥን በፊት ህዝቤ፣
አወጡልሽ ለሺያጭ፣
አቀረቡልሽ ለጨረታ፣
ለጣሊያን፣ ለእንግሊዝ፣
ለካናዳ፣ ላሜሪካ።

ልትመስይ ነው አሉ ጋናን፣
ልትሆኝ ላይቤሪያ፣

እልል በይ አገሬ፣ ያሳደግሽኝ፤
እልል በይ እማማ።

ይህን ነው የምንል እኛ፣
ቢወድቅልን የወርቅ ቅራፊ፣
ያምባሻ ፍርፋሪ፣
የወያኔ ትራፊ።

ይህን ነው የምንል እኛ።

አጋሰስ-፩ ፡ እነሱስ ምን ይሉናል?

አጋሰስ-፪፡ ምን ይፈጥራሉ ብለህ ሌላ፣
«ግሩም አጋሰስ አገኘን» ከማለት በቀር፣
« አገሩን ሸጦ 'ሚበላ።»

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፤ 4/4/1996 አእ

# ጉልበት

*«ሀይለኛ እየሄደ ያስገብራል የትም፣*
*መሬት የሁሉ ነች ባለቤት የላትም፡፡»*

*እሮሮ፣ ከበደ ሚካኤል፣ ፲፱፻፵፩*

ይህ መሰረታዊ እውነት ነው፣
አለም ከተጀመረ ያልተጣሰ፣
የፍጡር መተዳደሪያ፣
ወደደም አልወደደ፣
እንዲህ ተፋልሶ የማያውቅ ህግ፣
በጊዜ የተፈተነ፣
የስነ-ፍጥረት ሁሉ መሰረት ነው፣
የተከበረ የታመነ፡፡

፩ እና ፩ ሁለት መሆኑ፣
አለመጣሱ እንጅ፣ አለመፋለሱ፣
ከዚህ የጠለቀ እውነትነት የለውም፣
ሁለንተናዊ የሆነ፣
አለም ስታልፍ የማያልፍ፣
የበቃ፣ የተፈፀመ፡፡

ስለዚህ ላለንበት አለም፣
የእውነት መለኪያችን፣
አለመፋለስ አለመጣስ ነው፣
የይግባኝ ማቆሚያችን፡፡
ላለማችን፣ ለምናውቀው፣ ጉልበት፣
መሰረቱ ነው የእውነት፣
ስለወደድን የማናነግሰው፣
ስለጠላን የማናረክሰው፣
ጥንትም የነበር፣ አሁንም ያለ፣
ያልተጣሰ ነው፣ ያልተገሰሰ፡፡

ውብ ነገር ምንድን ነው?

የሚወስነው መመሪያ፣
        ጉልበተኛ ባምሳሉ፣
ውብ ይባላል፣ ውብ ይሆናል፣
        ከዚያም አያልፍ ነገሩ፡፡

ዴሞክራሲስ?

የሚፈሩሩ ሰዎች፣
        የሚያደርጉት ስምምነት፣
የሚፋቅ ነው፣ የሚሰረዝ፣
        ሚዛኑ ያጋደለ ለት፡፡
የጉልበት መስፈሪያው ሲያደላ፣
        ሲያዘነብል ወዳንዱ፣
ተፈጥሮም እኩልታውን ይቀይራል፣
        መከበር አለበትና ህጉ፣ የሚዛኑ፡፡
ጥሩ መጥፎ፣ ክፉ በጎ፣
የሚባል ነገር የለም፣
        የማይሽረው ጉልበት ከቶ፡፡
ስለዚህል
ጉልበት የናንተ ስትሆን፣
        እውነትን ስትፅፉ፣
ስታሸንፉ ብቻ ሳይሆን፣
        ስታስገብሩ ስትገዙ፣
ጭቆናው ሲከብዳችሁ፣
        ስታነቡ ስታለቅሱ፣

ያኔም!!

ያኔም ይህንን ህግ አስታውሱ፣
ይህንን ህግ እንዳትረሱ፡፡

---
ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 8/4/1995 አእ

# አጋሰስ

ትንኝ፣ ጥዋት ከእንቅልፍዋ ተነስታ፣
«እስቲ ይህን ወባ ላሰራጭ፣ ስራ አልፍታ፣»
ብላ አይደለም ደም የምትመጥ፣ ያንዱን፣
ስትጨርስ ሌላውን ወግታ።

ኑሮዋን ማሸነፉዋ ነው እስዋ፣
የለት እንጀራዋን፣ ማግኘትዋ።
ግን ወባን ለማጥፋት፣ ከምድር ገጥ፣
ትንኝዋን መግደሉ ነው የሚመረጥ።

«ምን አጠፋሁ እኔ፣
ወባ አይደለሁ ራሴ፣
ተሸከምኩ እንጅ በሽታውን፣
አሰራጨሁ እንጅ ወባውን፣
ሆኖብኝ ተፈጥሮዬ፣
ያርባ ቀን እድል፣ እጣዬ።»

ብላ ብትማፀን ትንኝዋ፣
አያድናትም ከሞት፣
የጠላት አጋሰስ ናትና።

---

ሴንት ሉዊስ ድሬ ዳያራ፣ 3/26/1996 አእ

# አንበሳ

ወዶ አይደለም ውሻ፣
ጌታውን ሲያይ፣
 ጭራውን የሚቆላ፡፡
ስቃዩን ስለቻለ፣
ክብሩን ለዘመናት ስለጣለ፣
ውርደት በደሙ ሰረፀ፣
ባርነትም ተፈጥሮው ሆነ፡፡

እኛም ባርነት ከሞቀን፣
ውርደት ከሆነ 'ማይከብደን፣
ለልጅ የሚሆን ደዌ እንተዋለን፣
ስናልፍ የማያልፍ አብሮ፣
 የማይሽረው፣ ሞታችን፡፡

ሳይጀመር በፊት ነው፣
 አሻፈረኝ ማለቱ፣
እንደ አንበሳ መኖሩ፣
 እንደ አንበሳ መሞቱ፡፡
እንደመኮንን፣ እንደአበራ፣
 እንደ አስራት ወልደየስ፣
እንደ ታየ፣ እንደቃሲም፣
 እንደ መነኩሴው አምሀየስ፡፡

ሳይጀመር በፊት ነው፤
 አሻፈረኝ ማለቱ፣
እንደ ሀጂ መሀመድ፣
 እንደ ስለሽ ሙላቱ፡፡

እንደ ሀሰን ልጅ፣
 እንደስጦታው፣
እንደ አደም፣ እንደአሊ፣
 እንደአሰገደች ሸዋንግዛው፣

እንደ ይስሀቅ፣ እንደ በለጠ፣
እንደ ፀጋየ ደብተራው፡፡
ሳይጀመር በፊት ነው፡፡

ሳይለመድ ፊት ውሻነቱ፣
ባህል ሆኖ ሳይቀር ውርደቱ፣

አሁን ነው ወቅቱ፣ ጊዜው፣
እምቢ መባያው፣
እንደ አንበሳ መኖሪያው፣
እንደ አንበሳ መሞቻው፡፡

አሁን ነው፡፡

---
ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 4/8/1998 አእ

# ማስታወሻ

የሚፃፍበት ደብተር ሀሳብ እንደመጣ፣
ማለት ነው፣ ሳይበተን ሳይጠፋ፣
አይመለስምና ከደበዘዘ፣ ከራቀ፣
ከሄደ፣ ከተረሳ፣ ከትውስታ አዘቅት ከወደቀ፡፡

ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 10/20/1995 አእ

# ትዝታ

*«ሞት አደላድሎኝ አፈር ካልተጫነኝ፣*
*ቃሌን አላጥፈውም፣ ካንቺ ጋር ነዋሪ ነኝ፡፡»*

ፈረንጆች፣
እየመነመነ ሲሄድ ተስፋቸው፣
እየጎላ ትዝታቸው፤
«እንዲያ ማድረግ አይችሉም፤
ከእንግዴህ!» ይላሉ፣
ያዩት፣ የሰሙትን ሁሉ፡፡

ዘፋኝ ተባዮቹ፣ ያሁኖቹ፣
ያዜሙ ይሆን፣ እንደተሾመ ምትኩ?
ተሾመም አይችል፣ ማዜም እንደተሾመ፣
ጥላሁንም ተሸነፈ፣ ሀብለ ድምፁ ደከመ፡፡

ያለፈው እየጠፋ፣
አዲሱ ሳይወለድ፣ ሽል ሆኖ እየቀረ፣
ለምለሙ አፈር ታጥቦ፣ አልቆ፣
ድንጋዩ ብቻ ቀረ፣
እርቃኑን፤
አግጦ፤
እየሳቀ፣

ነበርን ማለት ከሆነ ከንቱ፣
ምን ይዋጠን እኛን፣
አልጥም ያለን አዲሱ፤
አልታይ ያለን እድገቱ፣
ግስጋሴው ወደፊት፣
ነፃነት እኩልነቱ፡፡

ምን ይዋጠን?

ይቅርታህን ፀጋዬ፣
        አትታዘበን ቶሎ፣
የነበርንን ከንቱነት፣
        ያስተማርክ ብትሆንም ለኦቴሎ፤

እኛ ተሸነፍን በቃ፣
የምኞት ኑሮአችን አክትምዋል፣
                እንዳንጠግብ በተስፋ፣
ጉልበታችንም ደከመ፣
        መጭውን በሀይል እንዳንገዛ፣
ነበርን ብቻ ነው የቀረን፣
        የልብ ስእል ትዝታ።

ይቅርታህን ፀጋዬ፣
ኦቴሎ አበሻ አይደል፣
        እነመለስን መች አዩ።

---
ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ 8/10/1998 አእ

# አረንጉዋዴ

አረንጉዋዴ፣
　　　　የምወድሽ ቀለሜ፣
　　　　የማፈቅርሽ ቀለሜ፣
አረንጉዋዴ።

ምን አለ የማያምር፣
　　　　አንቺ ከነካሽው፣
　　　　በአስማታዊ እጆችሽ ከዳሰስሽው፣
　　　　በአስማታዊ አይኖችሽ ካየሽው።
አረንጉዋዴ።

---

ናዝሬት-ኢትዮጵያ፣ 1968-1974 አእ

# ኩነኔ

የለ አይሉ፣ አለ፤
አለ አይሉ፣ የለ፤
ህልም አይባል ነገር፣ ህልም አይደለ፣
እውን አይሉት፣ አያጠግብ እውንነቱ፣
ለሚያስቡ፣
ለሚያስተውሉ።

የጠፋ ነገር መጨበጫው፣
መቆለፊያው፣
ወይ መክፈቻው፤

ረቂቁ ሚስጥር ሲገለፅ፣
እንቆቅልሹ ሲፈታ፣
አለመገኘት ነው መኮነን፣
መገለል ከደስታ።

ናዝሬት-ኢትዮጵያ፤ 1968-1974 አእ

# ምን አለ?

ምን ጣፋጭ ነገር አለ፣
ከምናውቀው፣
        መኖርን የመሰለ፣
ከህይወት የተሻለ፣
ምን አለ?

---

ናዝሬት-ኢትዮጵያ፤ 1968-1974 አእ

# ታውቀዋለህ ካለህ

ካለህ እውነት፣
እንደሚሉት፣
የምጠይቅህን አስረዳኝ፣
የምለምንህን አድለኝ።

«አትፈትነኝ!» አትበለኝ።

ካልፈተንኩህ፣
እንዴት ልመንህ?
አላየሁህ፣
አልሰማሁህ።

«ተፅፎልሀልም!» አትበለኝ።

እውነት ካለህ፣
ታውቀዋለህ፣
የተፃፈ እንደማይታመን፣
የተጫረ እንደማይታመን፤

ታውቀዋለህ፣
ካለህ።

---

ናዝሬት-ኢትዮጵያ፣ 1968-1974 አእ

# እኔነቴ

ማን ነኝ እኔ፣
ምንድን ነው እኔነቴ?
ቂመናዬ፣
ሰውነቴ፣
ወይስ አንጎሌ፣
        ጭንቅላቴ፡፡

ሀሳቤ ነው እኔነቴ፣
        ፍላጎቴ፣
        ጭንቀቴ፣
        ምኞቴ፡፡

የምኖር ከሆነ፣
        ያለሀሳብ፣
        ያለጭንቀት፤
በሌሎች ምኞት፣
በሌሎች ፍላጎት፣
እኔ እኔ አይደለሁም፤
        የለሁም፡፡

---

ናዝሬት-ኢትዮጵያ፣ 1968-1974 አእ

# የመኖር ትርጉሙ

የምወደውን አጣሁ፣
የምመኘውንም አጣሁ፣
ችግር ንቆ ተወኝ፣
ደስታም ተሰወረኝ፣
ሸሸኝ፡፡

ባይሰለቸኝም ገና ኑሮ፣
ጠፋብኝ ፍችው፣
ውበቱ፡፡

ምንኛ መታደል ነው፣
ተቸግሮ ማልቀስ፣
መጨነቅ፤
ምንኛ መታደል ነው፣
ኑሮን መጥላት፣
የሚጠሉት ነገር ማግኘት፣

ወይም፣
ምንኛ መታደል ነው፣
መደሰቱ፣
የሚወዱት ነገር ማግኘቱ፡፡

ካልወደዱ፣
ወይ ካልጠሉ፣
ምንድን ነው፣
የመኖር ትርጉሙ?

---

ናዝሬት-ኢትዮጵያ፤ 1968-1974 አእ

# ሌብነት እስኪቀር

ጥሩ ነገር ስታገኙ የሚያምር፣
ብትሸጡት የሚያከብር፣
ውድ እቃ ስታገኙ የሚያጉዋጉዋ፣
የሰው አይን የሚያርፍበት፣
ተውት አትጠቀሙበት፣
ደብቁት፣
ቅበሩት።

ለመበልፀግ ለማጌጥ፣
ይቅርባችሁ ማሰቡ፣
ንብረታችሁን ማስከበር፣
ዘራፊን መቁዋቁም እስክትችሉ።

ግን እኮ ከተገኘ ውድ እቃ፣
እውነትን የሚያስረሳ የሚያታልል፣
እምን ውስጥ ይሸሸጋል?
ከዬትስ ይደበቃል?

ባይገኝ ይሻላል፣
ከጅምሩ፣
እውቀታችሁ እስኪከበር፣
ቁጣችሁን ሰምተው እስኪፈሩ።

---

ናዝሬት-ኢትዮጵያ፣ 1968-1974 አእ